# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

**_Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)_**

(አንድነት/United)


## የኢህአዴግ ውሳኔና የኢትዮ-ኤርትራ ጉዳይ

ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ. ም
June 19, 2018

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ከኤርትራ ጋር አዲስ የሰላም ኑሮ ጅማሮ አስፈላጊ ስለመሆኑ ግንቦት 28 ድርጅታቸው የወሰነውን ውሳኔ ተመርኩዘው መግለጫ ሰጥተዋል። አስከትለውም ሰኔ 11 በፓርላማው ውስጥ ጉዳዩን ይበልጥ አብራርተዋል።

መግለጫው ድርጅታቸው ኢህአዴግና መንግሥታቸው እስካሁን ድረስ በተግባር ያልፈጸመውን በሕዝባችንም እጅግ የተወገዘውን "የአልጀርስ ስምምነትና የሄጉን የድንበር የማካለል ውሳኔ" በመባል የሚታወቁትን ይዘተ-ብልሹ ውሳኔዎች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሚቀበልና ከኤርትራ ገዥ ቡድን ጋርም ለድርድር ዝግጁ እንደሆኑ ይገልጻል። ይህ ውሳኔ እጅግ የሚያሳዝን ቢሆንም ተስፋ የሚሰጠው ግን ጠ/ሚኒስትሩ ጉዳዩ የተዘጋ እንዳልሆነና የመጨረሻው ውሳኔ የሕዝብ መሆኑን ለፓርላማው መግለጣቸው ነው።

ድርጅታችን ኢሕአፓ (አንድነት)ም ሆነ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከላይ በተጠቀሱት የህወሓት-መራሹ ውሳኔዎች ላይ ያለን መሠረታዊ ተቃውሞና ልዩነት በግልጽ የታወቀ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በድንበር አካባቢ ነዋሪ በሆነው ሕዝብ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ ሀገራችን አሁን ከምትገኝበት እጅግ የተወሳሰቡ ችግሮች አኳያ ሲታይ በዚህ ጉዳይ የመጨረሻ እልባት ለማስገኘት አሁኑኑ አጣዳፊ ውሳኔ የሚሻ ጉዳይ ነው ብሎ ድርጅታችን አያምንም።

የኢትዮጵያ መንግሥት ዋነኛ ሃላፊነት የሀገሩንና የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ጥቅም ማስጠበቅ ሆኖ ወቅቱ ሲደርስ ምን መደረግ እንደሚገባ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ድርጅቶችና የድንበሩ አካባቢ ኢትዮጵያውያን በጉዳዩ ሃሳባቸውን የሚገልጹበትና የሚወስኑበት መድረክ ማመቻቸትን ይጠይቃል።


**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**

ይህን የኢህአዴግን ውሳኔ ተከትሎ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ሰኔ 6፣ 2010 ዓ. ም በጉዳዩ ላይ አስገራሚና በተቃርኖ የተሞላ መግለጫ አውጥቷል። መግለጫው ህወሓት የአልጀርሱን ስምምነት እንደሚቀበል ይገልፅና ጠ/ሚ አብይ ውሳኔውን እንዳለቀ ጉዳይ አድርገው ለሕዝብ መግለፃቸውን ይቃወማል። አስገራሚው ጉዳይ ኢህአዴግ ውሳኔውን ሲያስተላልፍ ዘጠኝ የህወሓት አመራር አባላት በስብሰባው ተሳትፈዋል። ከዚያም አልፎ ህወሓት በብርጌድ የታገዘ ኃይል በመላክ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠልና እውቅናም ባስቸኳይ እንድታገኝ የተባበሩት መንግሥታትና ዓለምአቀፍ ማኅበረሰቡን ሲወተውት የነበረው ህወሓት እንደሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ሃቅ ነው።

በተጨማሪም የህወሓት መሪዎች ከሻእቢያ ጋር አብረው ኢትዮጵያን ሲቦጠቡጡ ኖረዋል። ያለ ወደብ ያስቀሯትን አገር በጦርነት ማግደው ከመቶ ሺህ በላይ ዜጎች ካለቁ በኋላ አሳፋሪውን የአልጀርስ ውል ፈረሙ። ይህ ሁሉ እየታወቀ በጠ/ሚ አብይ የተጀመረውንና ሕዝባዊ ድጋፍ ያገኘውን ለውጥ ለመቃወሚያ ህወሓት ዛሬ የኤርትራን ጉዳይ አጀንዳ አድርጎ ብቅ ማለቱ አሳፋሪ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንኛውም መልኩ መሠረታዊ ጥቅሙንና ሉዓላዊነቱን በሚፃረር ስምምነት ላይ ለሚያሳየው ህጋዊ ተቃውሞ ኢሕአፓ (አንድነት) ከጎኑ እንደሚቆም እያረጋገጥን፣ ህወሓት የኢትዮ-ኤርትራን ጉዳይ አስታክኮ የሚያነሳቸው ለውጥ አደናቃፊ ሃሳቦች ገና ከጅምሩ ይዟቸው ከተነሳቸው ለውጥ አጋች አጀንዳዎች አንዱ በመሆኑ ድርጅቱ የሚያደርገውን ፀረ-ለውጥ እንቅስቃሴ አጥብቀን እንቃወማለን።

ድል ለአኢትዮጵያ ሕዝብ!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**